| | |
|---|---|
| **በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከፈል ክፍያን ለመወሰን የወጣ**<br><br>**የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ መመሪያ ቁጥር 1053/2017**<br><br>**ሚያዝያ 1 2017 ዓ.ም** | **Ethiopian Investment Board Directive**<br><br>**On Fee Rates Payable for Services Provided by the Ethiopian Investment Commission No.1053/2025**<br><br>**April 9/2025** |
| በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ ቁጥር 1322/2016 አንቀፅ 23 መሰረት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ይህን መመሪያ አውጥቷል።<br><br>1. <u>አጭር ርእስ</u><br><br>ይህ መመሪያ **'በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከፈል ክፍያን ለመወሰን የወጣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ መመሪያ ቁጥር 1053/2017'** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።<br><br>2. <u>የአገልግሎት ክፍያ</u><br><br>በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ ቁጥር 1322/2016 አንቀፅ 23 ንኡስ አንቀፅ (2) መሰረት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሚጠይቀው የአገልግሎቶች ክፍያ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ላይ በተመለከተው መሰረት ይሆናል።<br><br>3. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u><br><br>ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመስግቦ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ድህረ-ገፅ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል። | This Directive is issued by the Ethiopian Investment Board pursuant to Article 23 of the Special Economic Zone Proclamation No.1322/2024.<br><br>1. <u>**Short Title**</u><br><br>This Directive may be cited as the **'Ethiopian Investment Board Directive on Fee Rates Payable for Services Provided by the Ethiopian Investment Commission No.1053/2025'**.<br><br>2. <u>**Service Fees**</u><br><br>Service fees to be charged by the Ethiopian Investment Commission pursuant to sub-article (2) of Article 23 of Proclamation No.1322/2024 shall be as prescribed by the schedule attached hereto.<br><br>3. <u>**Effective Date**</u><br><br>This Directive shall come into force as of the date on which it is posted on the web pages of the Ministry of Justice and the Ethiopian Investment Commission. |
| **የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ቦርድ**<br><br>**አዲስ አበባ**<br>**ሚያዝያ, 2017 ዓ.ም** | **Ethiopian Investment Board**<br>**Addis Ababa**<br>**April, 2025** |
| | . |

ክፍል 1፡ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በአንድ ማእከል ማእቀፍ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚከፈል ክፍያ

**Part 1: Fee Rates Payable for Services Provided by the Ethiopian Investment Commission Within the One Stop Shop**

| | የአገልግሎት አይነት | የክፍያ መጠን (በአሜሪካ ዶላር) | TYPE OF SERVICE | FEE (USD) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የቪ.አይ.ፒ መስተንግዶ አገልግሎት ደብዳቤ | 155 | VIP Services Support Letter | 155 |
| 2. | የመሬት ልማት ስምምነት ማረጋገጥ | 50 | Notarization of Land Development Agreement | 50 |
| 3. | ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ መስጠት | 50 | Issuance of Title Deed for SEZ Enterprise | 50 |
| 4. | በልዩ ኢኮኖሚ ዞን የግንባታ ዲዛይን ማፅደቅ | 150 | Design Approval (SEZ) | 150 |
| 5. | በልዩ ኢኮኖሚ ዞን የግንባታ እና መጠቀም ፈቃድ መስጠት | 150 | Issuance of Construction and Use Permit Inside SEZ | 150 |
| 6. | በልዩ ኢኮኖሚ ዞን የግንባታ እቃዎች ዝርዝር ሰነድ ማፅደቅ | 100 | Approval of Bill of Quantity (SEZ) | 100 |
| 7. | የድርጅት/ካምፓኒ ስም ምዝገባ | 50 | Registration of Business, Company Name | 50 |
| 8. | የድርጅት/ካምፓኒ ስም መቀየር/ማሻሻል | 50 | Alteration, Amendment of Business/Company Name | 50 |
| 9. | የንግድ ስም ምዝገባ | 50 | Trade Name Registration | 50 |
| 10. | የንግድ ስም ማሻሻል፡ መለወጥ፡ መተካት | 50 | Amendment, Change, Substitution of Trade Name | 50 |
| 11. | የመመስረቻ ወይም መተዳደሪያ ፅሁፍ ማረጋገጥ፡ ማሻሻል፡ መቀየር | 25/በቅጂ | Notarization, Amendment, Change of Memorandum or Articles of Association | 25/copy |
| 12. | የባለአክሲዮኖች ውሳኔ/ቃለጉባኤ ማረጋገጥ | 25/በቅጂ | Notarizing Shareholders' Resolution, Minutes | 25/copy |
| 13. | ትክክለኛ ግልባጭ (ኮፒ) ሰነዶችን ማረጋገጥ | 25/በቅጂ | Ascertaining Copy Documents | 25/copy |
| 14. | የንግድ ምዝገባ መስጠት፡ ማሻሻል፡ መተካት፡ መቀየር፡ መሰረዝ | 50 | Issuance, Amendment, Replacement, Substitution, Cancellation of Commercial Registration | 50 |
| 15. | የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት (አዲስ) | 50 | Issuance of Investment Permit (New) | 50 |
| 16. | የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ፈቃድ መስጠት | 50 | Issuance of Expansion or Upgrading Investment Permit | 50 |
| 17. | የአዲስ/የማስፋፊያ ኢንቨስትመንት ፈቃድ እድሳት | 50 | Renewal of (New/Expansion) Investment Permit | 50 |
| 18. | የኢንቨስትመንት ፈቃድ መለወጥ/ማሻሻል | 25 | Change, Amendment of Investment Permit | 25 |
| 19. | የኢንቨስትመንት ፈቃድ መተካት | 25 | Issuance of Substitute Investment Permit | 25 |
| 20. | የኢንቨስትመንት ስራ ለውጥ | 25 | Investment Activity Change | 25 |
| 21. | የኢንቨስትመንት ፈቃድ መሰረዝ | 25 | Cancellation of Investment Permit | 25 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 22. | ነባር ድርጅት መግዛት | 100 | Acquisition of Existing Enterprise | 100 |
| 23. | በትግበራ ላይ ያለ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ማስተላለፍ | 100 | Transfer of Investment Project Under Implementation | 100 |
| 24. | የኢንቨስተሮች ማህበር ምዝገባ | 200 | Registration of Investors' Association | 200 |
| 25. | የኢንቨስተሮች ማህበር ምዝገባ እድሳት | 50 | Renewal of Registration of Investors Association Registration | 50 |
| 26. | የስራ ፈቃድ መስጠት | 100 | Issuance of Work Permit | 100 |
| 27. | የስራ ፈቃድ እድሳት | 80 | Renewal of Work Permit | 80 |
| 28. | የስራ ፈቃድ ትክ/መሰረዝ | 50 | Substitution, Cancellation of Work Permit | 50 |
| 29. | የዘገየ የስራ ፈቃድ እድሳት፡ መሰረዝ | 50 | Late Work Permit Renewal, Cancellation | 50 |
| 30. | የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ምዝገባ/ሰርቲፊኬት መስጠት፡ የምዝገባ እድሳት | 50 | Registration, Issuance of Certificate for Technology Transfer Agreement; Renewal | 50 |
| 31. | የቴክኖሎጂ ሽግግር ሰነድ ማረጋገጥ | 50 | Technology Transfer: Authentication of Document | 50 |
| 32. | ከወጭ ንግድ ጋር በተያያዘ የውጭ ድርጅት የካፒታል መዋጮ ሳይኖረው የሚያደርገው ትብብር ምዝገባ፡ እድሳት፡ | 50 | Registration of Export-oriented Non-equity Based Foreign Enterprise Collaboration; Renewal of Registration; | 50 |
| 33. | ወደ አገር የገባ የመጀመሪያ/ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ካፒታል ምዝገባ፡ ማሻሻያ | 50 | Registration of Initial/Additional Investment Capital Brought into Country | 50 |
| 34. | የትርፍ ካፒታል ምዝገባ | 50 | Registration of Capital Plowing Back (Appropriated Profit) | 50 |
| 35. | የኢንቨስትመንት ካፒታል ምዝገባ ማሻሻያ ደብዳቤ | 25 | Registration of Investment Capital - Amendment Letter | 25 |
| 36. | የንግድ ስራ ፈቃድ መስጠት (የአዲስ ወይም የማስፋፊያ ኢንቨስትመንት) | 100 | Issuance of Business License (New/Expansion Investment) | 100 |
| 37. | የንግድ ስራ ፈቃድ እድሳት | 75 | Renewal of Business License | 75 |
| 38. | የንግድ ስራ ፈቃድ ማሻሻያ፡ መሰረዝ፡ | 50 | Amendment, Cancelation of Business License | 50 |
| 39. | የዘገየ የፈቃድ እድሳት (ሁሉም) | 25 | Late License Renewal (All) | 25 |
| 40. | ለሁሉም የጉምሩክ እና ቀረጥ ነፃ ፈቃድ ሙሉ አገልግሎት | 20/ለጥያቄ | Custom Duty-Free Permissions (All) | 20/request |
| 41. | የገቢ ግብር ነፃ መብት ድጋፍ ሙሉ አገልግሎት | 25 | Income Tax Holiday Permit Full Support Service | 25 |
| 42. | የካፒታል እቃዎች፡ ተሽከርካሪዎች፡ ግንባታ እቃዎች ዝውውር ፈቃድ አገልግሎት | 25 | Permission for Transfer of Capital Goods, Vehicles and Construction Materials | 25 |
| 43. | ለባንክ ዋስትና ድጋፍ ደብዳቤ (ቀረጥ ነፃ እቃዎች) | 25 | Support Letter for Bank Guarantee - Duty Free Items | 25 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 44. | በቫውቸር ስርአት የጥሬ እቃዎች ዝውውር | 25 | Transfer of Raw Materials: Voucher System | 25 |
| 45. | የተመላሽ ቀረጥ ድጋፍ አገልግሎት | 25 | Duty Drawback Service | 25 |
| 46. | የኪሣራ ማስተላለፍ ድጋፍ አገልግሎት | 25 | Loss Carried Forward | 25 |
| 47. | ለተለያዩ ተቋማት የሚፃፍ የድጋፍ ደብዳቤ፡ሌሎች ጁሪዲካል አገልግሎቶች | 15 | Support Letter to Various Offices, Other Juridical Services | 15 |
| | | | | |

**ክፍል 2: የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በድሬዳዋ ነፃ ንግድ ቀጠና (እና ተመሳሳይ ቀጠናዎች) ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚከፈል ክፍያ[1]**

**Part 2: Fee Rates Payable for Services Provided by the Ethiopian Investment Commission Within the Dire Dawa Free Trade Zone (and Similarly Designated Zones)**

| | የአገልግሎት አይነት | የክፍያ መጠን (በአሜሪካ ዶላር) | TYPE OF SERVICE | FEE (USD) |
|---|---|---|---|---|
| 48. | አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት (የሚከተሉትን ክፍሎች አካቶ) | 1000 | A) Issuance of New Investment Permit (including the following components) | 1000 |
| (ሀ) | የድርጅት/ካምፓኒ ስም ምዝገባ፡ መቀየር፡ ማሻሻል፡ | | B) Company Name Registration, Amendment, Substitution; | |
| (ለ) | የውጭ ምንዛሪ አካውንት ለመክፈት የድጋፍ ደብዳቤ | | C) Letter to Open Foreign Exchange Account | |
| (ሐ) | የመመስረቻ ወይም መተዳደሪያ ፅሁፍ ማረጋገጥ፡ | | D) Notarization of Memorandum and Articles of Association | |
| (መ) | የመመስረቻ ወይም መተዳደሪያ ፅሁፍ ማሻሻል፡ መቀየር | | E) Amendment of Memorandum and Articles of Association | |
| (ሠ) | የባለአክሲዮኖች ውሳኔ/ቃለጉባኤ ማረጋገጥ፡ ማሻሻል፡ መቀየር | | F) Notarizing Shareholders' Resolution, Minutes (incl. Changes, Amendment) | |
| (ረ) | ትክክለኛ ግልባጭ (ኮፒ) ሰነዶችን ማረጋገጥ | | G) Ascertaining Copy Documents | |
| (ሰ) | የንግድ ምዝገባ መስጠት፡ ማሻሻል፡ መተካት፡ መቀየር፡ መሰረዝ | | H) Issuance, Amendment, Replacement, Substitution, Cancellation of Commercial Registration | |
| 49. | ማሻሻያ (የሁሉም) (ኢንቨስትመንት ፈቃድ፡ የካምፓኒ ስም ምዝገባ፡ የመመስረቻ ወይም መተዳደሪያ ፅሁፍ፡ ቃለጉባኤ፡ የንግድ ምዝገባ፡ ወዘተ) | 50 (ተመሳሳይ) | Amendments: All (Investment Permit, Company Name Registration, Memorandum/Articles of | 50 (flat) |

[1] በዚህ ክፍል በግልፅ ከተመለከቱት ውጭ ለሚጠየቁ አገልግሎቶች የሚተገበረው የክፍያ አሰራር በክፍል 1 ላይ በተቀመጠው ዝርዝር መሰረት ይመራል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | Association, Minutes, Commercial Registration etc.) | |
| 50. | የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ/ማሻሻያ ፈቃድ መስጠት | 500 | Issuance of Investment Permit: Expansion/Upgrading | 500 |
| 51. | የአዲስ/የማስፋፊያ ኢንቨስትመንት ፈቃድ እድሳት | 500 | Renewal of (New/Expansion) Investment Permit | 500 |
| 52. | የስራ ፈቃድ መስጠት | 500 | Issuance of Work Permit | 500 |
| 53. | የስራ ፈቃድ እድሳት | 300 | Renewal of Work Permit | 300 |
| 54. | የስራ ፈቃድ መተካት/መሰረዝ | 100 | Substitution, Cancellation of Work Permit | 100 |
| 55. | የዘገየ የስራ ፈቃድ እድሳት፡ መሰረዝ | 100 | Late Work Permit Renewal, Cancellation | 100 |
| 56. | የዘገየ የፈቃድ እድሳት (ሌሎች ሁሉም አገልግሎቶች) | 100 | Late Permit/License Renewal (All Others) | 100 |
| 57. | የግንባታ ዲዛይን ማፅደቅ | 500 | Construction Design Approval | 500 |
| 58. | የግንባታ እና መጠቀም ፈቃድ መስጠት | 500 | Issuance of Construction and Use Permit | 500 |
| 59. | የግንባታ እቃዎች ዝርዝር ሰነድ ማፀደቅ | 300 | Approval of Bill of Quantity | 300 |
| 60. | የሊዝ/ንኡስ ሊዝ ስምምነት ምዝገባ፡ የባለመብትነት (ባለቤትነት) ሰነድ መስጠት፡ | 100 | Registration of Lease/Sub-lease Contract; Issuance of Title Deed | 100 |
| 61. | የኢንቨስተሮች ማህበር ምዝገባ፡ እድሳት | 100 | Registration of Investors' Association; Renewal; | 100 |
| 62. | የነፃ ንግድ ቀጠና መግቢያ ፓስ (ለድርጅቶች፡ እንግዶች) | 25 | Free Zone Gate Pass (Enterprises, Guests) | 25 |
| 63. | የንግድ ስራ ፈቃድ መስጠት (አዲስ) | 1000 | Business License: New | 1000 |
| 64. | የንግድ ስራ ፈቃድ (እድሳት) | 750 | Business License: Renewal | 750 |
| 65. | የንግድ ስራ ፈቃድ (ማሻሻያ) | 100 | Business License: Amendment | 100 |
| 66. | የንግድ ስራ ፈቃድ (ማሻሻያ/ማስፋፊያ ኢንቨስትመንት) | 300 | Upgrading/Expansion Business License | 300 |
| 67. | ተስማሚነት/ጥራት ደረጃ አገልግሎቶች | 100 | Conformity/Quality Related Services | 100 |
| | | | | |